# የሞንትጎመሪ ካውንቲ የዜግነት ክፍያዎች እንዳይጨመሩ በመቃወም በፌደራል ሕግ ክስ ከመሰረቱት ጋር ተቀላቅሏል፤ የካውንቲው ዋና ስራ አስፈጻሚ (ኤግዚኩቲቭ) ኤልሪክ መስፈርቱን የሚያሙሉ ነዋሪዎች አሁን እንዲያመለክቱ ያበረታታሉ።

*ለአስቸኳይ ጋዜጣዊ መግለጫ፡ መስከረም (ሴፕቴምበር) 24 , 2020*

የካውንቲ ዋናሥራ አስፈፃሚ (ኤግዚኩቲቭ) ማርክ ኤልሪክ ሞንትጎመሪ ካውንቲ ከ 33 የአሜሪካ ከተሞች እና አውራጃዎች እንዲሁም ከአሜሪካ ከንቲባዎች ስብስብ ጋር በመሆን የዜግነት ህግ ፕሮጀክትን አስመልክቶ የአሜሪካ የአገር ውስጥ ደህንነት ጥበቃ መመሪያን ተቃውሞ አጭር መግለጫ((አሚከስ ብሪፍ) ማቅረቡን አስታውቋል ። ክሱ ለአዲሱ የዩናይትድ ስቴትስ ዜግነት እና ኢሚግሬሽን አገልግሎቶች (ዩ.ኤስ.ሲ.አይ.ኤስ) ፖሊሲ ምላሽ ለመስጠት ነው ፣ ብቁ ለሆኑት ነዋሪዎች ለዜግነት ጥያቄ እንዲሁም ለሌሎች የሕግ ደረጃዎች እና ጥቅሞች ማመልከትን የበለጠ ውድ ያደርገዋል ። ክሱ የፌደራል ፍ / ቤትን ይህን አዲስ ህግ ተግባራዊ ከመሆን እንዲያስቆም እየጠየቀ ነው ።

እ.ኤ.አ. ከጥቅምት (ኦክቶበር) 2 ጀምሮ ዩ.ኤስ.ሲ.አይ.ኤስ ለዜግነት ማመልከቻ የሚከፈለው ወጪ ከ 725 ዶላር ወደ 1,200 ዶላር ጨምሯል እንዲሁም ለሁሉም ዝቅተኛ ገቢ ላላቸው ነዋሪዎች የክፍያ ማንሳትን ፍቃድ አስወግዳል ። ዩ.ኤስ.ሲ.አይ.ኤስ የቋሚ መኖሪያ ፍቃድ (ግሪን ካርድ) የማመልከቻ ክፍያንም በመጨመር እና የጥገኝነት ጥያቄ ማመልከቻ ክፍያ ተግባራዊ በማድረግ አሜሪካን ከአራት አገሮች አንዷ እንድትሆን ያደርጋታል ።

የካውንቲው ዋና ሥራ አስፈፃሚ (ኤግዚኩቲቭ) ኤሊሪክ "የስደት (ኢሚግሬሽን) ክፍያዎችን በእጥፍ በማሳደግ እና ዝቅተኛ ገቢ የማግኘት መብትን በማስወገድ ለአሜሪካ ዜግነት ለማመልከት ብቁ ሆነው ግን ወጪውን መሸፈን የማይችሉትን ብዙዎችን የማስቀረት አቅም ሊኖረው ይችላል" ብለዋል ። "የአሜሪካ ዜግነት ለመክፈል አቅም ላላቸው ብቻ መወሰን የለበትም ። አዳዲስ ዜጎችን ለመቀበል በአቅማችን የተቻለንን ሁሉ ማድረግ አለብን ፣ በመንገዳቸው ላይ እንቅፋቶችን ማስቀመጥ አይደለም" ። የአሜሪካ ዜጋ ለመሆን የሀብት ፈተና መፍጠር ከአሜሪካውያን እሴቶቻችን ጋር የሚጋጭ ነው ።

ህጋዊ ቋሚ ነዋሪዎች የአሜሪካ ዜጎ ች ሲሆኑ የእኛ አውራጃ ይለመልማል " አሉ ኤልሪክ ። ነዋሪዎቻችን ዜግነት የማግኘት ሂደቱን (ፕሮሰሱን) ክፍያው ከማደጉ በፊት በአፋጣኝ እንዲጀምሩ እና የህግ ምክርን እና የዜግነት ማመልከቻ እገዛን ከታወቁ አገልግሎት ሰጭዎች ብቻ እንዲፈልጉ እናሳስባለን ።

በሞንትጎመሪ ካውንቲ ውስጥ በአሁኑ ጊዜ በግምት 56,000 ለአሜሪካ ዜግነት ብቁ የሆኑ ነዋሪዎች ይገኛሉ ። በመላው አሜሪካ በአሁኑ ወቅት ለአሜሪካ ዜግነት ብቁ የሆኑ 8.8 ሚሊዮን ሕጋዊ ቋሚ ነዋሪዎች አሉ ።

በዜግነት መርሃግብሮች እና አገልግሎቶች ላይ ጥያቄ ያላቸው ነዋሪዎች የጊልክሪስት የስደተኞች መርጃ ማዕከልን በ 240-777-4940 ማነጋገር ወይም ድህረ ገፃቸውን በ www.montgomerycountymd.gov/Citizenship መጎብኘት ይችላሉ ።

ቆጠራዎን"ካውንት" በሞንትጎመሪ ካውንቲ ውስጥ ያስቀምጡ! የህዝብ ቆጠራውን በኦን ላይን ፣ በስልክ ወይም በፖስታ ማጠናቀቅዎን እርግጠኛ ይሁኑ ። ደህንነቱ የተጠበቀ ፣ በምስጥር የሚያዝ ፣ ቀላል እና አስፈላጊ ነው።
# 2020 የሕዝብ ቆጠራ # ሁሉም ሰው ይቆጠራል ሞንትጎመሪ ካውንቲ ሜሪላንድ

###

የህዝብ መረጃ ቢሮ ሰልኩ 240-777-6507